# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ፕሮግራም

**ህዳር 2012**

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በነፃና ርቱዓዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሊመሠረት እንዲችል፣ አባላቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ትግልና ሂደት ከፍተኛውን መስዋዕትነት የከፈሉት አባላቱ የወደቁለት ክቡር ዓላማ እውን እንዲሆን፣ ተጠያቂነትና ግልጽነትን የተላበሰ ዴሞክራሲያዊ አሠራር በድርጅቱና በሀገራችን ውስጥ እንዲሰፍን እራሱን እንደገና መርምሮና ሰላማዊና ሕጋዊ ትግልን የሚመጥን መዋቅራዊ መሻሻሎችን አድርጎ፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን ዳግም አድሶ፣ በአዲስና በተሻለ አሠራር ትግሉን ለማስቀጠል የበለጠ ተዘጋጅቷል።

ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ከሚያዝያ 1964 ዓ. ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባት፣ እኩልነት የሰፈነባትና ዜጎች በመፈቃቀድ አብረው የሚኖሩባት ሉዓላዊነቷን የጠበቀች ሀገር በሁሉም መስክ ለመገንባት የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር ታግሏል፣ አታግሏል፣ አሁንም እየታገለ ይገኛል። ኢሕአፓ ከምሥረታው ማግሥት ጀምሮ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ሦስት አገዛዞችን አጥብቆ የታገለ ሲሆን ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱም አገዛዞቹ የኢትዮጵያን ሕዝብ መብት ረግጠውና አፍነው በአምባገነንነት የቀጠሉ መሆናቸውና ጨርሶም ሕዝብ የሚፈልገውን ለውጥ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆናቸው ነው።

ከ29 ዓመታት በፊት በሀገራችን ለሥልጣን የበቃው ገዥ ኃይል ጠባብ ብሄረተኛ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በብሄረሰብ ከፋፍሎና አናክሶ ሊገዛ ይሁነኝ ብሎ የወሰነ አምባገነን ቡድን ነው። ይህ ቡድን በሥልጣን እስካሁን የቆየው በሕዝብ ድጋፍ ሳይሆን ሕዝብን በትክክል በማይወክል በተጭበረበረ ምርጫ እና የወታደራዊና የደህንነት ኃይሉን በመጠቀም፣ ተቃውሞን ሁሉ በኃይል እያፈነ በመቀጠሉ ነበር። የጥፋት ዓላማውን ከማሳካት ያደናቅፉኛል ብሎ የገመታቸውን እንደ ኢሕአፓ ያሉ ድርጅቶችን እስከዛሬ ድረስ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ሕጋዊ ሆነው እንዳይንቀሳቀሱ አገዶ ኖሯል።

አስተሳሰቦቻቸውን በህገ-መንግስቱ ላይ ፍጹም ቦታ እንዳይኖራቸው በማድረግ የአንድ ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም ብቻ ሕገ መንግሥት ተብሎ እንዲወጣ ሆኗል። ይኸው ጠባብ ብሄርተኛ አገዛዝ እንዲለወጥ፣ የሕዝብን ድምፅ እንዲያከብር፣ የሰላምና ዕርቅ መንገድ እንዲመርጥ፣ ሀገርን ብጥብጥ ውስጥ ሊያስገቡ ከሚችሉ ከፋፋይ ፖሊሲዎችና ተግባራት እንዲቆጠብ በተደጋጋሚ ጥሪ ቢደረግለትም፣ አልሰማችሁም ብሎ በማንአለብኝነት ከመቀጠሉም በላይ በሕዝብ ላይ የሚያደርስውን አፈና በማጠናከርና የሀገሪቱን ማንኛቸውንም ተቋማት እንደመጨቆኛ መሣሪያነት በመጠቀም የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን፣ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞችን፣ ለመብታቸው የታገሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎችን ለእሥርና ለሞት ዳርጎ ቋይቷል። ይህም በመሆኑ፣ መንግሥታዊው ሽብር፣ አድሎና ጭቆና ያስመረረው ሕዝብ ወደ አደባባይ በመውጣት፣ ላለፉት ሦስት ዓመታት ሀገሪቱን ባጥለቀለቀ ሁኔታ ተቃውሞውን በከፍተኛ እምቢተኛነት አሳይቷል። ሕዝባዊ እምቢተኛነቱ በአገዛዙ ላይ በፈጠረው መጠነ-ሰፊ ተቃውሞ ምክንያትም በአገዛዙ በራሱ ውስጥ የለውጥ አራማጆች እንዲፈጠሩና በሕዝብ ድጋፍ ታጅበው ወደ ሥልጣን እንዲመጡ ሆኗል። ይህም በመሆኑ ተስፋ ሰጭ የለውጥ ምልክቶች እየታዩ እንደሆነ ኢሕአፓ ተገንዝቦ ወደ አገር ውስጥ የገባና ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራት የደረሰ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜያት ጀምሮ የተከሰተው ችግር እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

ይህ አሁን የተጀመረው የለውጥ ጅማሮ ሳይደናቀፍ ሁሉንም አሳታፊ በሆነ መንገድ ሀገሪቱን ወደ ዘላቂ ስላምና የተረጋጋ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች የማሸጋገር ዕድል እንዳለፉት ጊዜያት ተሰናክሎ እንዳይቀር፣ ኢሕአፓ የሚጠበቅበትን ሁሉ ያደርጋል።

በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የዴሞክራሲና የፍትኅ ተቋማት በኢህአዲግ ፍጹም ቁጥጥር ሥር ሆነው እንዳለፈው የሚቀጥሉበት ሁኔታ ተቀባይነት እንደሌለው ታውቆ፣ በዲሞክራሲያዊ ተቋማት ሕዝብ አመኔታ ሊኖረው ወደሚችልበት ደረጃ ላይ ለማድረስ የሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፎ የግድ ይላል። ሁለንተናዊ በሆነ መልክ የለውጡ ሂደት ግቡን እንዲመታም ከተፈለገ በሀገሪቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ መግባባት የግድና አስፈላጊም ነው። በመሆኑም ሁሉንም አሳታፊ የሆነ የብሔራዊ የውይይትና የእርቅ ጉባዔ መጠራት እንዳለበትም አጽንዖት መስጠት እንፈልጋለን። ይህ ጉባዔ እውን እንዲሆን ኢሕአፓ አጋር ከሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመሆን ይሠራል።

በመሣሪያ ኃይል ታግዞ ሥልጣን ላይ የወጣው ኢሕአዴግ፣ ኢሕአፓንና በሀገር አንድነት ዙሪያ ተመሳሳይ አመለካከታ ያላቸውን ሌሎች ድርጅቶችን ከፖለቲካው ሂደት በማግለል፣ በራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም አንፃር ብቻ የቀረጸው ሕገ-መንግሥት ሀገሪቱን እጅግ አደገኛ ወደሆነ የርስ በርስ ግጭትና ቀውስ ላይ እንዳደረሳት እያየን ነው። ይህም በመሆኑ፣ ባለፈው እንደተደረገው ሳይሆን፣ ማንም ሳይገለል፣ በሁሉም ባለድርሻዎች ሙሉ ተሳትፎ፣ ሕገ-መንግሥቱ ሊሻሻል ወይንም አዲስ ዘገመንግሥት ለወጣ ይገባዋል ብሎ ኢሕአፓ በጽኑ ያምናል። ለተፈፃሚነቱም ይታገላል።

ለ29 ዓመታት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የተደረገው የጥቃት ዘመቻ ቆሞ ኢትዮጵያዊነት፣ ሀገራዊ አንድነት፣ አካታችነት፣ መቻቻልና አብሮነት እንዲያገግሙ ብዙ ሥራ መሠራት አለበት። በመሆኑም፣ በዚህ አንፃር ኢሕአፓ አስፈላጊውን ሁሉ ትኩረት ስጥቶ ከሁሉም ለውጥ አራማጅ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ይሠራል። አገዛዙ ሲከተለው በቆየው ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጩ ፖሊሲዎች ምክንያትም ይሁን በቀደምት ቅሬታዎችና መቀያየሞች፣ በሀገሪቱ ቀጣይ የሆነ የሰላምና የብሔራዊ ዕርቅ ሥራ መሠራት እንዳለበት ኢሕአፓ ያምናል። ይህን ሥራ የሚሠራ ብሔራዊ የሰላምና ዕርቅ ኮሚሽን መቋቋሙን እይደገፍን የተቋሙ ነፃነት ተጠብቆ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ይገቡ ዘንድ ኢሕአፓ ጥሪ ያቀርባል።

ለዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ አቢይ ሆነው የቆዩ የሕዝብ ጥያቄዎች ዛሬም ያለጥርጥር ምላሽ የሚሹ ናቸው። ስለሆነም ኢሕአፓ ቀደም ሲል መሬት ላራሹ፣ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም፣ የሀገርና የሕዝብ ሉዓላዊነት ይከበር፣ አንድነት በዴሞክራሲና በእኩልነት መሠረት ላይ ይረጋገጥ፣ የሠራተኛው መብት ይከበር፣ ለወጣቶች ሥራ ይፈጠር፣ የሴቶች እኩልነት ይረጋገጥ፣ ፍትኅና የሕግ የበላይነት ይስፈን፣ የሃይማኖት እኩልነት ይከበር …ወዘተ የሚሉ መሪ መፈክሮችን በማንገብ ዛሬም ትግሉን ቀጥሏል።

ኢትዮጵያ ከገባችበት የድህነትና የመከራ ማጥ መውጣት የምትችለው በዜጎቿ ሁሉ ጥረትና ቆራጥ ትግል በመሆኑ ኢሕአፓ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በተካተቱት መሠረታዊ አቋሞች ዙሪያ ሕዝብን አስባስቦ ለማኅበራዊ ፍትህና የዜጎች መብት እንዲከበር በሰላማዊ መንገድ ለመታገልና ለማታገል ጥረቱን ይቀጥላል።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከህዳር 27 እስከ ህዳር 28፣ 2012 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ውስጥ ባካሄደው ጉባዔ፣ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታና ድርጅቱ ያለበትን ሁኔታ በጥልቀት ከመረመረ በኋላ የሚሻሻለውን አሻሽሎ ሰላማዊ ትግሉን በሀገር ቤት ለማድረግ የሚያስችለውን ይህንን የፖለቲካ ፕሮግራምም አጽድቋል። የተሻሻለው ፕሮግራም የኢሕአፓን ራዕይ፣ አቋሞችና ዓላማዎች የሚያንጸባርቅ ነው። ዘላቂ ሕዝባዊ ድል ለማረጋገጥም ከሌሎች መሰል አመለካከት አራማጆች ጋር ያብራል፣ ከዚያም ከፍ ባለ ደረጃ ይሠራል።

## አንቀጽ አንድ

### ራዕይ

የዜጎች የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች የተጠበቁባት፣ ድህነትን፣ ረሃብንና መታረዝን ከምድሯ ያጠፋች፣ ፍትኀዊነትና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጅ ዕድገቷና በልማት ክንዋኔዋ ከሌሎች የዓለም ታላላቅ ሃገሮች እቻ የደረሰች፣ ሰላም የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ ፍትኅ የተረጋገጠባት ታላቅ ኢትዮጵያን መፍጠር።

### ዓላማ

ኢሕአፓ የሚከተሉትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ የማህበራዊና የዲፕሎማሲያዊ/የውጭ ግንኙነት ዓላማዎች ለማሳካት ያላሰለሰ ትግል ያደርጋል፡፡

1.1 በፓርቲው ርዕዮተ ዓለምና ፕሮግራም መሠረት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ በምርጫ በመወዳደር የኢትዮጵያን ህዝብ ለመንግሥት ስልጣን ማብቃት፣
1.2 የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በፈጣን የእድገት ጎዳና የሚመራበትን ስልት መቀየስ፣
1.3 አገር በቀል የሆኑ ባለሃብቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሰፋ ያለ የኢኮኖሚ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን መንገድ ማመቻቸት፣
1.4 በሳይንስና ቴክኒዎሎጂ ዘመም የሆነ የኤኮኖሚ መሠረት ከሌሎች ዘርፎች ጋር ጎን ለጎን መዘርጋት፣
1.5 ሁሉም ዜጋ በሃገሩ ሠርቶ የሚኖርበት ሁኔታ ማመቻቸት፣ እኩል የሥራ ዕድል መፍጠር፣
1.6 ትምህርት ዕድሜያቸው ለደረሰ ዜጎች ሁሉ እንዲዳረስ ማድረግ፣

1.7 የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችል፣ ለምጣኔ ሀብቱ ዕድገት በእዉቀትና ብክህሎት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ሊያመነጩ፤ ሊፈጥሩና ሊሰጡ፣ በውቀትና በክህሎት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ሊያመነጩ፤ ሊፈጥሩና ሊሰጡ፤ ግብዓት ሊሆኑ በሚችሉ ዘርፎች የሰለጠነ የሰው ሃይል መፍጠር፣

1.8 የሀገሪቱ ብሄራዊ እና የሥራ ቋንቋ ከሁለት ያላነሰ ሆኖ ወደፊት አብዛኛው ህዝብ የሚጠቀምባቸውን ቋንቋዎች ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በማጣጣም እንዲጨመሩ ይሠራል፣

1.9 ዜጎች ማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ማድረግ፣

1.10 የመንግሥት አሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ሙስናን መታገል፣

1.11 ነፃና የርስ በእርስ ቁጥጥር የሚኖርበት የመንግሥት አካላት (ዘግ አውጭ፣ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈፃሚ) መገንባት፣

1.12 የዜጎችን የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ማድረግ፣

1.13 አስተማማኝ የሆኑ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መዘርጋት፣ ተደራሽነታቸው ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ፣

1.14 የጎዳና ተዳዳሪነትን እና ሴተኛ አዳሪነትን የመሳሰሉ ማህበራዊ ችግሮችን ማስወገድ፣

1.15 የህዝብን አሰፋፈር መልክአ ምድራዊ አሰፋፈር፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እና የመልማት አቅም፣ ታሪካዊ ትስስር፣ ስነልቦናዊ መስተጋብር፣ የመግባቢያ ቋንቋ፣ መሠረት ያደረገ ፌደራላዊ የመንግሥት አደረጃጀት ማድረግ፣

1.16 የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም የሚያስከብር የዜኘት፣ የኢኮኖሚ፣ የህዝብ ለህዝብ ዲፕሎማሲ ፖሊሲ እንዲኖር ማድረግ፣

1.17 የውሃ ሀብታችንን፣ ድንበር ተሻጋር ውንዞቻችንን ጭምር ባዓለም አቅፍ የውሃ ህግ መሠረት የህዝባችንን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣

1.18 በሁሉም መስኮች የሴቶችን የእኩልነት መብትና ተሳትፎ ማረጋገጥ

1.19 ወጣቶች በትንህርት፣ በጤና በኢኮኖሚ ተገቢ ሚናቸውን እንዲጫወቱ ማስቻል፣

1.20 በውጭ ኑሯቸውን ያደረጉ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ሁለንተናዊ ሁኔታ የሚያገባቸውና የሚገዳቸው በመሆኑ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ መሥራት፣

ከላይ የተጠቀሱትን መሠረት በማድረግ የኢ.ሕ.አ.ፓ ዓቢይ ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ምንጭነት በሕግ የሚረጋገጥበት፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የሕዝብና የሀገር አንድነት የሚጠበቅበት፣ የእምነትና የሃሳብ ነፃነት የሚከበርበት፣ በሕዝብ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋም መንግሥት፣ ማኅበራዊ ፍትኀን ግቡ ያደረገ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመሥረት ነው።

## አንቀጽ ሁለት

## የፖለቲካ ፕሮግራም

### 2.1. የሀገሪቱ ሕገ-መንግሥታዊ መሠረት የሕዝብን ይሁንታ ያገኘ መሆን ይገባዋል።

2.1 የሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች፣ የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎችና ወኪሎች፣ የሙያ ማኅበራት ተጠሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሕግ አዋቂዎች፣ የሀገር አዛውንቶች፣ በሙያቸውና በዕውቀታቸው ታዋቂነት ያገኙ ግለሰቦች....ወዘተ በሚሳተፉበት ሕገ-መንግሥታዊ ጉባዔ ተሻሽሎ ይረቀቃል ወይንም ይለወጣል፣

2.2 በሕገ-መንግሥቱ ረቂቅ ላይ ሕዝቡ በነፃና በስፋት ተወያይቶበት፣ የጎደለ ካለ ጨምሮ፣ የሚሻሻለውን አሻሽሎ፣ በመጨረሻ ሰነዱ በውሳኔ ሕዝብ ያጸድቃል፣

2.3 በሕገ-መንግሥቱ መሠረት በሕዝቡ ነፃና ርቱዓዊ የሆነ ጠቅላላ ምርጫ የሚቋቋመው መንግሥት የሥልጣን ዘመኑ የተወሰነ ይሆናል፣

2.4 ሕገ-መንግሥቱ የሚከተሉትን ዓበይት ሃሳቦችና መተክሎች ማካተት ይኖርበታል ብሎ ኢ.ሕ.አ.ፓ ያምናል። እነሱም፦

2.4.1 ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊ የሥልጣን ምንጭ መሆኑ፣

2.4.2 ሕግ አውጭው፣ የሕግ አስፈጻሚው የዳኝነት ሰጭው መንግሥታዊ ዘርፎች ሥልጣናቸው፣ ኃላፊነታቸው፣ ተግባራቸው በግልጽ ተለይቶ እንዲዋቀሩ፣

2.4.3 ኢ.ሕአፓ ባለ ሁለት አካል ምክር ቤት (ባይ-ካሜራል) እንዲመሠረት ይታገላል፣ የዚህ ምክር ቤት አንዱ አካል በሕዝብ ቁጥር ላይ ተመሥርቶ በዜጎች ቀጥተኛ ድምፅ የሚመረጥ ሲሆን ሌላው አካል (ሁለተኛው) ደግሞ፣ የፌደራሉ ሥርዓት ክፍለ ሐገራዊ አስተዳደሮች እያንዳንዳቸ እንደ ሕዝብ ብዛታቸው የሚወከሉበት፣ የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ማለትም ቁጥራቸው ዝቅተኛ የሆኑ (ህዳጣን) ብሄረሰቦች፣ ሴቶች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ፣ ሃይማኖቶችና ሌሎችም ባህላዊ ተቋሞች...ወዘተ እንዲወከሉ፣ የሚያደርግና የሕዝባችንንም የጋራ እሴቶች የሚያጠናክር ተቋም እንዲሆን ያደርጋል፣

2.4.4 የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን በዝርዝርና በግልጽ እንዲሰፍሩና እንዲረጋገጡ ያደርጋል፣

2.4.5 የብሄረሰቦች እኩልነትና የኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት፣ መልካዓ-ማኅበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ ትሥሥርን መሠረት ባደረገ ፌደራላዊ የክፍለ ሐገሮች ግንኙነት ላይ የተዋቀረ እንዲሆን ያስችላል፣

2.4.6 ዴሞክራሲ በተግባር የሚረጋገጥበት የፖለቲካ ሥርዓት እንዲመሠረት ይሆናል፣

2.4.7 ሕገ መንግሥቱን የሚተረጉም ነፃ ፍርድ ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል፣

2.4.8 በሕዝቡ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋሙ ፌደራላዊም ሆነ የክፍለ ሀገር ዴሞክራሲያዊ መንግሥታት የሥልጣን ዕድሜው አራት ዓመት እንዲሆን

2.4.9 የኢትዮጵያ ሀገራዊ ሉዓላዊነትና ድንበሮቿም የማይደፈሩና የማይገሰሱ መሆናቸው በሕገ-መንገሥቱ ውስጥ እንዲሰፍር ማድረግ፣

2.4.10 የማንኛውም ኢትዮጵያዊ የዜግነት መብት በሕግ ካልተገፈፈ በስተቀር፣ የተከበረ የማይደፈር መሆኑም እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

2.4.11 ትውልደ ኢትዮጵያውያን በኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከዜጎች ባልተለየ ሁኔታ የሚሳተፉበት የሕግ ማእቀፍ ማዘጋጀት።

## አንቀጽ ሦስት

## ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች

3.1 ወደፊት በምትመሠረተው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ውስጥ የሁሉም ዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ ማድረግ፣

3.2 የመናገርና የፅሁፍ ነፃነት፣ ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ፣ የሥራና የመኖሪያ ቤት የመምረጥና የመቀየር፣ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የመዘዋወር፣ ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆኑ የሙያና የብዙሃን ማኅበራት የመደራጀት፣ የፖለቲካ ድርጅት የማቋቋም ወይም በተቋቋሙት ውስጥ አባል የመሆን፣ የመምረጥና የመመረጥ፣ በኢትዮጵያ ሗላዊ ግዛት ውስጥ የመዘዋወር፣ መኖሪያ የመመሥረት፣ ንብረት የማፍራትና የግል ንብረት ባለቤት የመሆን፣ ቋንቋንና ባህልን የመጠበቅና የማሳደግ…ወዘተ መብቶች ማክበር፣

3.3 ከሃይማኖትና ከመንፈሳዊ ዕምነት ውጭ በፖለቲካ ፍልስፍናነትና መመሪያነት እስካልተጠቀመ ድረስና የዘር የበላይነትንም ሆነ የዘር ጥላቻን መሠረት እስካላደረገ ድረስ ማንኛውም ድርጅት ሕጋዊ ሕልውና ኖሮት በሰላም የመንቀሳቀስ መብቱን ማክበር፣

3.4 በሕገ-መንግሥቱ የሚደነገገውና ከመንግሥት ጣልቃ ገብነትና ቁጥጥር ነፃ የሆነ የዳኝነት ሥርዓት በተግባር እንዲውል ማድረግ፣ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑን ማረጋገጥ፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማንም ሰው ከ48 ሰዓት በላይ በማረፊያ ቤት እንዳይቆይና እንዳይታሠር፣ መኖሪያ ቤቱ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዳይፈተሽ፣ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት እስካልተረጋገጠ ድረስ በመከሰሱ ብቻ ንፁህነቱ እንዳይሻር፣ በዋስ የመለቀቅ መብቱ እንዲከበርለት፣ ጠበቃ እንዲያቆምና ከጠበቃውም ጋር የመገናኘት መብቱ እንዲጠበቅለት፣ ያለፍርድ ቤት ብያኔ የንብረት ባለቤትነት መብቱ እንዳይደፈር፣ ስልኩ እንዳይጠለፍ፣ ፖስታው እንዳይከፈት፣ የኢ-ሜይል ልውውጦቹ እንዳይታዩ፣ ያለፈቃዱ ንብረቱ የመንግሥት መገልገያ እንዳይሆን…ወዘተ ማድረግ፣

3.5 ሁሉም ዓይነት ኢ-ሰብዓዊ ተብሎ በሕግ የተደነገገ ቅጣት በፍጹም የተከለከለ ይሆናል። ኢ-ሰብዓዊ ቅጣት በዜጎች ላይ የሚፈጽሙ ማለትም በድብደባ ማሰቃየትን፣ በኃይል መያዝን የመሳሰሉትን የሚያደርጉ በሕግ እንዲጠየቁ ማድረግ፣

3.6 በዘር፣ በብሄረሰብ፣ በፆታ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ላይ ተመሥርቶ ማበላለጥ ወይም ማዳላት በሕግ እንዲከለከል ማድረግ፣

3.7 የዜጎች የግል መብቶችና የቡድን መብቶች ከተጋጩ የዜጎች መብቶች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፣

3.8 ማንኛውም ዜጋ ኢትዮጵያዊነቱን ለመተው ወይንም መልሶ ለማግኘት አይገደድም፣

3.7 ማንኛውም ዕድሜው 18 ዓመት የደረሰ ዜጋ የመምረጥ መብት፣ 25 ዓመት የሞላው ዜጋ ደግሞ የመመረጥም መብት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

## አንቀጽ አራት

### <u>የብሄረሰቦችን መብት ማክበርና ማስከበር፣ እኩልነታቸውን ማረጋገጥ</u>

4.1 ብሄረሰቦች በቋንቋቸው የመጠቀምና ባህላቸውን የማዳበር መብታቸው እንዲከበር ማድረግ፣

4.2 ብሄራዊ ቋንቋዎች እንደተጠበቁ ሆነው ክፍለ ሀገሮች በራሳቸው ቁዋንቁዋ መጠቀም ይችላሉ

4.3 በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ በሚኖራቸው ተሳትፎ፣ በማንኛውም ብሄረሰብ ላይ አድልዎ አለመኖሩን ማረጋገጥ፣

4.4 በኤኮኖሚ፣ በትምህርት፣ በጤና...ወዘተ ረገድ ለተጎዱ ወይም ለተረሱ ክፍሎች ልዩ ድጋፍ መስጠት።

4.5 በኢትዮጵያ ውስጥ ከአማርኛ ቀጥሎ በብዛት የሚነገር ቋንቋ (አፋን ኦሮሞ) ሁለተኛ ብሔራዊና የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ

## አንቀጽ አምስት

### መንግሥትና ሃይማኖት

5.1 በሀገሪቱ የዕምነት ነፃነትና እኩልነት ይከበራል፣ ሁሉም ሃይማኖቶች በሚከተሏቸው ምዕምናን ድጋፍና እርዳታ መንፈሳዊ ተልእኳቸውን የሚያሟሉ ይሆናሉ፣ ለሁሉም ሃይማኖቶች እኩል የሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፣

5.2 መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አይገቡም፣

5.3 የሁሉንም ዜጎች የሚፈልጉትን ዕምነት የመከተል ወይም ያለማመን መብት ያከብራል።

5.4 በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ሐይማኖት ላይ ጥቃት ሲደርስ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ ሕግን የማስከበር ግዲታ አለበት።

## አንቀጽ ስድስት

## የኢኮኖሚ ፕሮግራም

### ብሄራዊ ኤኮኖሚን መገንባት

ብሄራዊ ብልጽግናን መሠረት ያደረገ፣ የሀገሪቷን ሕዝብ ጥቅም ያማከለና ቅድሚያ የሰጠ፣ በማህበራዊ ፍትሃዊነት መርኅ ላይ የተመሠረተ የገበያ ኤኮኖሚ ሥርዓት በመፍጠር ዕድገትን፣ ማሕበራዊ እኩልነትን እና ዘለቄታዊነትን የሚያረጋግጥ ብሄራዊ ኤኮኖሚ መገንባትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል። የታለመው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መምጣቱን እና የኢትዮጵያን ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረጉን ማረጋገጥ፣ ከአጠቃላይ ዕድገት ባሻገር

አሳታፊነቱን የሚመለከት፤ ዕድገቱ ለድሀው በተለይም በገጠር ለሚኖረው ድሀ ሕዝብ በሚያመጣው ጠቀሜታ ላይ የሚያተኩር መሆኑን መለካት፡፡

## 6.1. በግብርና መስክ

6.1.1. የግብርናው ክፍል ለኢትዮጵያ ኤኮኖሚ የደም ሥር እንደመሆኑ መጠን ክፍለ ኤኮኖሚውን ለማሳደግ በሁሉም መስክ መጣር፣

6.1.2 አርሶ አደሮች በሚያርሱት መሬት ላይ የባለንብረትነት መብት ማለትም የመሸጥና የመለወጥ፣ የማውረስ፣ በዋስትና (በወለድ አገድ) የማስያዝ...ወዘተ ያላቸውን መብት ማክበር፣

6.1.3 መሬት አልባ አርሶ አደሮችን በመንግሥትና በኅብረተሰቡ ስምምነት ድጋፍ የሚታረስ መሬት በንብረትነት የሚያገኙበትን መንገድ መሻት፣

6.1.4 ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች ለማቋቋም ለሚሹና ለሚችሉ በግብርና ለሚተዳደሩ ግለሰቦች መንግሥት መሬት በረጅም ጊዜ የይዞታ ውል (በኮንሴሽን) ይሰጣል። የሚሰጠው መሬት መጠንና የይዞታው ውል (ኮንሴሽኑ) በሕግ ማስወሰን፡፡

6.1.5 የሀገሪቱን መሬት ከዓለም አቀፋዊ የመሬት ቅርምት በመጠበቅ በግብርናው ዘርፍ የሚደረጉ የሰፋፊ እርሻ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን መቆጣጠር፣ የገጠሩን ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ማረጋገጥ፣

6.1.6 መንግሥት የአርሶ አደሩ የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲልና ምርቱም እንዲዳብር ለአርሶ አደሮች አስፈላጊውን እርዳታና አገልግሎት (ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የሰብል ተባይ መከላከያ፣ የግብርና መሣሪያዎች...ወዘተ) ከቀረጥ ነፃ ማቅረብ፣ ገንዘብ ከእርሻ ብድር አገልግሎት (ባንክ) የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር፣

3.1.7. ግብርናው ከኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር እንዲቀናጅ፣ የከተማውና የገጠሩ የሥራ ዘርፎች እንዲደጋገፉ የግብርናው ዘርፍ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ጥሬ ዕቃ እንዲያቀርብ ኢንዱስትሪውም ለግብርናው ዘርፍ ግባቶችን እንዲያመርት ለገጠሩ ሕዝብም የሥራ መስክ እንዲፈጥር ማድረግ፣

6.1.8 ክፍለሀገራትን የሚያገናኙ መንገዶችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የህክምና ተቋማትን፣ የዕደ-ጥበባዊ ትምህርት አገልግሎት፣ የመስኖ ግድቦች፣ የቦዮች ሥራ ግል ጋሎት፣ የጥልቅ ጉድጓድ ውሃ…ወዘተ ማስፋፋት፣ እንዲሁም ማዳበሪያን ሊተኩ የሚችሉ የግብርናና የምርምር ዘዴዎችን ማበረታታት፣ ለግብርና ማዘመን እንዲውሉ ማድረግ፣ ሀገሪቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በምግብ ራሷን እንድትችል ማድረግ፣ በተለይ ድርቅ የሚያስከትለውን የውሃ እጥረት በትልልቅ የውሃ ግድቦች፣ የመስኖ ሥራዎች እንዲቋቋሙ፣ ድርቅን የሚቋቋሙ፣ አዝርዕቶች በምርምር እንዲፈጠሩ፣ ለሌሎቹም የእርሻ ግብዓቶች መሟላት ቅድሚያ እንዲሰጥ ማድረግ፣

6.18 በከፊል ወይም በሙሉ አርብቶ-አደር የሆኑትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ በሚቆዩባቸው አካባቢዎች መርዳት፣ ከተቻለም በፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ አመቺ በሆኑ ቦታዎች እያሠፈሩ በግብርና ሊሰማሩ ወይም በዘመናዊ መልክ የከብት እርባታ ሊያካሂዱ…ወዘተ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር፣ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች መስጠት፣

6.19 ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግድ፣ በትራንስፖርት፣ በባንክ፣ በፋይናንስ፣ በመድህን (ኢንሹራንስ)… ወዘተ ተቋማት ባለቤት መሆን በሕግ የተከለከለ ይሆናል።

## 6.2 በኢንዱስትሪ መስክ

6.2.1 የኢንዱስትሪው ክፍለ-ኤኮኖሚ በገበያ ኤኮኖሚ መርኅ መሠረት እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፣ ማበረታታት፡፡ሆኖም እንደኢትዮጵያ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች በውድድር ላይ የተመሰረተ የገበያ ኢኮኖሚ ሁሉንም ሕዝብ ተጠቃሚ የሚያደርግ ዕድገት ማምጣት ስለማይችል መንግሥት ግብይትን፣ ማብቃትን (empowerment) እና መልካም አስተዳደርን የማስፈን ጣልቃገብነት ሊኖረው ይገባል፣ ለዚህም፡

- ለሕዝብ ማህበራዊ ፍትሃዊነትን የሚያረጋገጥ፣ አካባቢን ከብክለት የሚጠብቅ እንዲሁም ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል ያለበት ጠንካራ እና ተፎካካሪ ቁሳዊ ብልጽግና ያለው ኢኮኖሚ መፍጠር

- ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን የሚያስችል የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ወቅታዊውን የዓለም ገበያ ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ተፎካካሪነትን ሊያመጣ የሚያስችል እንዲሆን
- የኢንዱስትሪ ፖሊሲው ሠራተኞች ብቃት ያላቸው እንዲሆኑና ከፍተኛ ክፍያ እንዲያገኙ የሚያግዝ መሆንና በኢኮኖሚው ልማት ውስጥ የሕዝቡን ተሳትፎ በማምጣት በአገር ውስጥ ገበያውም ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ መፍጠር እንዲችል፣
- በአጠቃላይ የኢኮኖሚው ዕድገት ማንንም አግላይ ያልሆነና በሂደቱ ተጎጂ የሚሆን የማህበረሰብ ክፍል እንዳይኖር ከፍተኛ ጥረትን የሚያበረታታ እንዲሆን ለማድረግ መንግሥት ሚናውን ይጫወታል፡፡

6.2.2 ለሀገሪቱ ብሄራዊ ጥቅም በጣም አስፈላጊ ሆነው በመገኘታቸው፣ ለግል ባለሀብቶች እንደሞዴል ሊታዩ የሚችሉ ከፈተኛ የቴክኖሎጂ አቅም ባላቸው የኢንዱስትሪ ፕሮጀክትቶች፣ ወይም የግል ባለሃብቶች ሳይሰማሩባቸው ቀርተው በመንግሥት ቁጥጥር፣ አስተዳደር ሥር እንዲውሉ ከተደረጉት በስተቀር በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የግል ባለንብረትነት መብት እንዲከበር ማድረግ፣ በሀገር ውስጥ ያሉ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪው መስክ ተሳትፏቸው እንዲጠነክር መደገፍ፣ ማበረታታት፣ የተመጣጠነ የቀረጥ ሥርዓት በማውጣት የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን መደገፍ፣

6.2.3 ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሠረተ ልማቶችን ማሳደግ፣ ብቃትና ተደራሽነት ያላቸው የፋይናንስ ተቋማት እንዲፈጠሩ ማድረግ፣ ባለሃብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ የሚያበረታቱ የመሬት ፖሊሲ፣ ለኢንዱስትሪ ሥራ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን የሚያፈሩ ተቋማትን መገንባት፣

6.2.4 የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ከሀገሪቱ የኤኮኖሚ ጥቅም ጋር በማይጋጭ መንገድ በሀገሪቷ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ በተለያዩ የኤኮኖሚ ዘርፎች የሥራ መስኮች እንዲሰማሩ ማበረታታት፣

6.2.5 ኢንዱስትሪዎችና ፋብሪካዎች ስርጭት ፍትሃዊ ማድረኛ ጥሬ ዕቃዎች በሚገኙባቸው ሊያሠሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ባሉባቸው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲቋቋሙ ማበረታታት፣ መርዳት።

## 6.3. በአገልግሎት ዘርፍ

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ከዝቅተኛው የዕድገት ደረጃ ወደ ከፍተኛው ሲያድግ መዋቅራዊ ለውጥ ማድረጉ አይቀሬ ነው፡፡ የኸውም ባደጉት አገሮች ምርትና ሠራተኛ ከቀዳሚው ግብርና ወደ ተከታዩ ኢንዱስትሪ መሄዱን ያመላክታል፡፡ ባደጉት ሀገራት የኢኮኖሚ ዕድገት በቀዳሚነት የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ የነበረው የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ቦታውን ለኢንዱስትሪው ሲለቅ በሦስተኛ ደረጃ የመጣው ደግሞ የአገልሎት ዘርፉ ነበር፡፡ በማደግ ላይ ባሉት ሀገሮች ግን ከዚህ የተለመደ የዕድገት አካሄድ አፈንግጠው ከግብርናው የኢኮኖሚ ዕድገታቸው፤ የኢንዱስትሪ ልማት ሂደትን በአግባቡ ሳያካሂዱ፤ ምርትና የሥራ መስክ ከግብርናው ዘርፍ በቀጥታ ወደ አገልግሎት ዘርፉ ይሸጋገራል፡፡

በመሆኑም በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች (ከሰሀራ በታች የሚገኙ ሀገሮችን ጨምሮ) የአገልግሎት ዘርፉ ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ውስጥ እያደገ የሚሄድ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በቅርብ ጊዜ እየታየ ባለው የአፍሪካ አህጉር የኢኮኖሚ ዕድገት በዚሁ የአገልግሎት ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ ስለዚህም የአገልግሎት ዘርፉን በተመለከተ የሚነሳው ጥያቄ በዘርፉ አስፈላጊነት ላይ ሳይሆን እንዴትና በምን ፍጥነት ዘርፉ ማደግ እንደሚገባው በመወሰኑ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም፡

- የአገልግሎት ዘርፉ ዕድገት ከግብርናው እና ከኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚዎች ጋር የሚኖረውን ተያያዥነት ማረጋገጥ
- በተለይም የማከፋፈል አገልግሎት ዘርፍ አመቺ እንዲሆን ማድረግና ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ ግንዛቤ ማዳበር

## 6.3.1 ንግድን በሚመለከት

6.3.1.1 የሀገር ውስጥ ገበያ ለማስፋፋት፣ ነጋዴዎችን ለማበረታታት በልዩ ልዩ የሀገሪቷ የኤኮኖሚ ዘርፍ የሸቀጥ ምርት ልውውጥ እንዲዳብር ማበረታታትና ድጋፍ መስጠት፣

6.3.1.2 ወደ ሀገር የማስገባትና ወደ ውጭ የመላክ ንግድን በተመለከተ በዋናነትና በቀዳሚነት የሀገሪቷ የግል ባለሀብቶች ነፃ ሆነው እንዲሠሩ ማበረታታትና ድጋፍ መስጠት፣

6.3.1.3 ለውጭ ንግድ የሚሆን ምርት በገበያ ኤኮኖሚ መርኅ ላይ በመመሥረት የአገር ውስጥ ፍጆታና የመመገብ አቅም በማይፃረር መንገድ ለማሳደግ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ማበረታታት፣

6.3.1.4 ሕገወጥ ንግድን ለማስወገድ አስፈላጊና ተጨባጭ የሆኑ እርምጃዎች መውሰድ፣ በጣም አነስተኛ በሆኑ እንደ ጉልት ገበያ ዓይነት ባሉ የኤኮኖሚ ዘርፎች ተሰማርተው ኑሯቸውን የሚገፉ ዜጎችን ወደ ከፍተኛ ኤኮኖሚ ለማሳደግ መጣርና መርዳት፣

6.3.1.5 የተባበሩት መንግሥታት፣ የአፍሪካ ኅብረት ወይም ሌሎች ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለምአቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ማዕቀብ ካደረጉባቸው አገሮች በስተቀር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ንግድ ከማንኛውም አገር ጋር እንዲካሄድ ማድረግ።

6.3.1.6 ሸቀጦችን ሆን ብለው ከገቢያ እንዲወጡ በማድረግ ወይም በመደበቅ የገቢያ ዋጋን በሚያናጉ ነጋዴዎች ላይ መንግሥት ክትትል አድርጎ እርምጃ ይወስዳል

## 6.3.2. ትራንስፖርትና መገናኛን በሚመለከት

6.3.2.1 ትራንስፖርትና መገናኛ ለገበያ መስፋፋት፣ ለአጠቃላይ ብሄራዊ ኤኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም ለሕዝብ ግንኙነትና ትስስር ብሎም ለሀገር አንድነት ማጠናከሪያ ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያደርግ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፣

6.3.2.2 መንግሥት መንገዶችን፣ የባቡር ሐዲዶችን፣ አውሮፕላን ጣቢያዎችን…ወዘተ በመሥራት፣ የባህር ትራንስፖርት እንዲሁም የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎት በመስጠት በዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሟላ ማድረግ፣

6.3.2.3 በቅርብና በሩቅ የሕዝብና የዕቃ ማጓጓዣ ከፍተኛ እጥረት በመኖሩ መንግሥት በዚህ ሥራ ለሚሰማሩ ኢትዮጵያውያን አስፈላጊውን ማበረታቻ ያደርጋል፣

6.3.2.4 ኢትዮጵያ ለገቢና ለወጭ ዕቃዎች ዝውውር የራሷ ወደብ እንዲኖራት መንግሥት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፤ለብሔራዊ ድህንነት የባህር በር ታደራጃለች፡፡

## 6.3.3 የባንክና የመድኅን (Insurance) ድርጅቶችን በሚመለከት

6.3.3.1 ብሔራዊ ባንክን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ማድረግ፣

6.3.3.2 መንግሥት በየጊዜው በሚያወጣው ዝርዝር ሕግ መሠረት የግል ባለሀብቶች በመድኅን (Insurance)ና በባንክ ሥራዎች እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የሚኖራቸው ተሳትፎ ዝርዝር ሁኔታዎችን በሕግ ማረጋገጥ፣ ተሳትፏቸው እንዲዳብር ማበረታታት።

## 6.3.4. የከተማ ቦታና ቤቶችን በሚመለከት

6.3.4.1 ማንኛውም ሰው የከተማ ቦታ በግል ንብረትነት የመያዝና ቤት የመሥራት፣ የማከራየት፣ የመሸጥና የመለወጥ፣ የማውረስ፣ በወለድ አገድ የማስያዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፣

6.3.4..2 የኪራይ ቦታ እጥረትን ለመቀነስ መንግሥት አቅሙ በፈቀደለት ተገቢ እርምጃዎችን ለመውሰድ ይጥራል፣ ባለሀብቶች የሚከራዩ ቤቶችን፣ የቁጠባ ቤቶችን… ወዘተ እንዲሠሩ ያበረታታል፣

6.3.4.3 የተወረሱ ቤቶችን በሚመለከት ከመንግሥትና ከሕዝቡ የተወጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ተጠንቶ ብዙሃኑን የማይጎዳና የባለንብረቶችን ጥቅምም ያገናዘበ መፍትሄ እንዲሰጠው ይረዳል።

# አንቀጽ ሰባት

# ማህበራዊ ፕሮግራም

## የዜጎችን ጥቅምና ደኅንነት ማስጠበቅ

7.1 በቀዳሚነት የዜጎችን ሁሉ ጥቅምና ደህንነት ማስጠበቅ፣

7.2 የሠራተኛ ማኅበራት ተወካዮችንም በማሳተፍ የሠራተኛ ሕግ ማውጣትና በሥራ ላይ ማዋል፣

7.3 የሠራተኞችን የመደራጀት መብት ማስከበር፣ የሙያ ማኅበራትን ነፃነት ማስጠበቅ፣ የሠራተኞችን የሥራ ማቆም አድማ መብት ማስከበር፣ ከመንግሥትና ከግል ባለሀብቶች ጋር ለተሻለ የሥራ ሁኔታ፣ ለደመወዝ ጭማሪ፣ ለአደጋ ዋስትና፣ ለጡረታ አበል ክፍያ፣ ለነፃ ህክምና ዋስትና....ወዘተ የመደራደር መብታቸውን ማረጋገጥ፣

7.4 ከ16 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው ልጆች በፋብሪካዎችና በማዕድን መቆፈሪያ ሥፍራዎች ተቀጥረው እንዳይሠሩ በሕግ መከልከል፣

7.5 የሠራተኞች መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን ከ8 ሰዓት እንዳይበልጥና በሳምንት ለ48 ሰዓታት የማረፍ መብት እንዲጠበቅላቸው ማድረግ፣

7.6 ሠራተኞች በቂ የሆነ የሕመም፣ የሕክምና፣ በማኅበራዊ ተግባሮች የመሳተፊያ፣ የሥራ ፈቃድ እንዲሁም የዓመት ዕረፍት እንዲያገኙ ማድረግ፣ ሴቶች ሠራተኞች አራት ወር የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ ክፍያ ጋር እንዲያገኙ ማድረግ፣

7.7 የሠራተኞች የመነሻ ደመወዝ የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም በሚያስችል ሁኔታ የሀገሪቱን የኤኮኖሚ አቅም ከግምት በማስገባት በሠራተኞችም ችሎታ ላይ ተመሥርቶ መወሰን፣ ከኑሮ ሁኔታው ጋር ማስተካከልና ማሳደግ፣

7.8 ሠራተኛው ሥራ-አጥ በሚሆንበት ጊዜ የሀገሪቷ አቅም በሚፈቅደው መሠረት ሊረዳ የሚችልበትን መንገድ መሻት፣ ሥራ-አጥነትን ለመቀነስ መጣር፣

7.9 በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉና ለጉዳት የተዳረጉ ዜጎች ዕርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ መፈለግ፣

7.10 ተፈላጊው ሙያ ያላቸው የሀገሪቱ ዜጎች እስካሉ ድረስ የሥራ ቦታ በቅድሚያ ለኢትዮጵያውያን እንዲሰጥ ማድረግ፣

7.11 የሀገሪቱ ዜጎች በረሃብ፣ በጥማትና እርዛት፣ በወረርሺኝ፣ በዘመኑ ቀሳፊ በሽታ (ኤይድስ)፣ በወባ፣ እንዲሁም በመጠለያ እጦት የሚደርስባቸውን ጉዳቶች አደጋ

ለማሰወገድ በመከላከል በሕይወት የመኖር ዋስትና እንዲኖራቸው ቅድሚያ ሰጥቶ ከፍተኛና ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ፣

7.12 ዜጎች የምግብ ዋስትና እንዲያገኙ ማድረግ፣ መሠረታዊ የሆኑትን የምግብ እህሎች ምርት አቅርቦት አቅም ለማሳደግ፣ ለምግብ አቅም ግንባታ ልዩ ትኩረት መስጠት፣ በአጭርና በረጅም ጊዜ እቅዶች ከፋፍሎ ተግባራዊ ማድረግ።

## አንቀጽ ስምንት

### <u>የሀገር እድገት ብልጽግናን መሠረት ያደረገ የትምህርት ሥርዓት ማቋቋም</u>

የትምህርት ሥርዐቱ ተግባራዊ የሚደረገው በፌደራላዊ ሪፐብሊክ አስተዳደር ሃላፊነት ክፍለ ሐገራዊ አስተዳደር ሃላፊነት ይሆናል። የፌደራል መንግሥቱ ሃላፊነት መሠረታዊ መብቶችን መደንገግና የትምህርት ጥራቱ፤ ደረጃውን የጠበቀ ይሆናል። በሁሉም ክፍለ ሐገሮች የትምህርት አሰጣጡና 6ኛ፤ የ8ኛ እና የ12ኛ ክፍል የመልቀቂያ ፈተና በፈደራል መንግሥቱ ደረጃ እንዲሆን ማድረግ። ዝርዝር ሃላፊነት ግን የክፍለ ሐገሮች አስተዳደሩ ጋር በመነጋገር ይሆናል። ስለዚህ ፌደራላዊ አስተዳደሩ በእያንዳንዱ እርከን ያለው ሥርዓተ-ትምህርት አገልግሎት ከብሄራዊ ፖሊሲው ጋር አለመጋጨቱን ያረጋግጣል።

8.1 ትምህርት ከአገሪቷና ከሕዝቧ ታሪክ፣ ባህልና ልምድ እንዲሁም ከፍላጎት ጋር ተቀናጅቶ የሚራመድበት መንገድ መፈለግ፣ ከምርት ሥራ እንዳይነጠል ማድረግ፣ መሃይምነትን ማጥፋት፣ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ለማስተማር በሕግ መደንገግና ተግባራዊ ማድረግ፣

8.2 የሥርዓተ-ትምህርት ፕሮግራም ዝግጅትን በተመለከተ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የተረቀቀ ብሄራዊ የትምህርት ፖሊሲ በሥራ ላይ ማዋል፣

8.3 የነፃ ትምህርት ዕድል እንዲስፋፋ መጣር፣ የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች፣ የማታ ትምህርት ቤቶች፣ የክረምትና የዩኒቨርስቲ ትምህርት ማስፋፋት፣

8.4 በሀገሪቷ ክፍሎች ሁሉ የሚካሄዱትን ትምህርታዊ ዕቅዶች ማስተባበር፣

8.5 የትምህርት ዕድል ሳያገኙ ለቆዩ ክፍሎች የተለየ ትኩረት መስጠት፣ ብቃት እያላቸው በችግር ምክንያት ትምህርት ለሚያቋርጡ ድጋፍ ለመስጠት መጣር፣

8.6 ለተንቀሳቃሽ የአርብቶ-አደር ልጆች ተስማሚ የትምህርት ግልጋሎት መስጠት፣

8.7 የመምህራን የሥራ፣ የሥልጠናና የደመወዝ ሁኔታ ማሻሻል፣ መርዳት፣ የተመቸ የሥራ አካባቢ ሁኔታ ማረጋገጥ፣

8.8 የተማሪዎችና የመምህራን በነፃ የመደራጀት መብት መጠበቅ፣ ትምህርታዊ ተቋሞች ከመምህራንና ከጠበብቶች በተወጣጡ ኮሚቴዎቸ እንዲተዳደሩ ማድረግ፣

8.9 የቴክኒክ፣ የሳይንስ፣ የግብርና....ወዘተ ትምህርትን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማስፋፋት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ተቋሞች፣ ሊቃውንት፣ ለኪነጥበብ ሰዎች፣ ለደራሲያን...ወዘተ እርዳታ ማድረግ፣ ግኝቶች፣ የፈጠራ ውጤቶች በሙከራ ላይ ያሉ የአዕምሮ ሥራዎች የባለቤትነት መብት በህግ እንዲጠበቅ ማድረግ፣

8.10 ስለተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ፣ ስለደንና ልማት፣ የነፋስ፣ የፀሐይና ሌሎችም የኃይል ማመንጫ ዘዴዎች እንዲሁም የዓለም የአየርና የየብስ ብክላ መከላከያ ዘዴዎች በሃገሪቱ ሥርዓተ-ትምህርት ልዩ ትኩረት እንዲሰጣቸውና እንዲካተቱ ማድረግ፣

8.11 መንግሥት ለሕፃናት የተለየ እንክብካቤ በማድረግ አቅሙ በፈጠነ መጠን የመዋዕለ ሕፃናት፣ የህክምና አገልግሎት ተቋሞች ማቋቋም ማበረታታት፣ መርዳት፣

8.12 የግል ትምህርት ቤቶች በሀገሪቱ ሕግ መሠረት በትምህርት ዘርፍ በበቂና በስፋት የሚሳተፉበት ሁኔታ መፍጠር፣ጥራታቸውን መቆጣጠር፤ ሕፃናት የአንደኛ ደረጃ የመጀምሪያ ሳይክል ትምህርታቸውን በአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ማድረግ። ከ5ኛ እስከ 8ኛ በብሔራዊ ቋንቋዎች የሚማሩ ሆኖ ከ9ኛ ክፍል በላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይማራሉ፡፡ ሁለቱ ብሔራዊ ቋንቋዎች እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጧቸዋል፡፡

8.13 ኢትዮጵያዊያን አንድነታቸውን እንዲያጠነክሩ የጋራ የሆነውን ታሪክ እንዲያውቁ በሁሉም ት/ቤቶች የኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ ይሰጣል፡፡

8.14 በሁሉም ትምህርት ቤቶች ሀገራዊ አንድነት እንዲያግዝ ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቻ በተጨማሪ ብሄራዊ የሥራ ቋንቋ የሆነው አማርኛንና ሌሎች ተጨማሪ ቋንቋዎችን እንዲማሩ ማድረግ፣

8.15. የትምህርት ሥርዐቱ በምርምርና ሥርጸት ላይ ተመስርቶ የኢትዮጵያን ችግሮች የሚያቃልል የሰው ኃይል በመፍጠር ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣

## አንቀጽ ዘጠኝ

### የጤና ጥበቃ አገልግሎት ተቋማትን ማስፋፋት

9.1 የሕዝብን ጤና ለመጠበቅ የጤና ጥበቃ አገልግሎቶችን በገጠርና በከተማ በሚገባ ማስፋፋት፣ በገጠር ክሊኒኮችንና የጤና ጣቢያዎችን ማስፋፋት፣ ተላላፊ በሽታዎችን በተቀነባበረ ዘመቻ በክትባት ማጥፋት፣ የጤና ባለሙያዎችን በብዛት ማሠልጠን፣

9.2 አቅም የሌላቸው ዜጎች በነፃ ሊታከሙ የሚችሉበትን መንገድ መፍጠር፣ ለእናቶችና ለህጻናት ልዩ ትኩረት መስጠትና መንከባከብ

9.3 ሀገር በቀል የሆኑትን ባህላዊ የህክምና ዘዴዎችና መድሃኒቶች በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር እየተደገፉ በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

9.4 የግል ሐኪም ቤቶች፣ ክሊኒኮችና ሆስፒታሎች በሀገሪቷ የጤና ጥበቃ ሕግ መሠረት በስፋት የሚሳተፉበትን ሁኔታ መፍጠር፣ ትክክለኛ ግልጋሎት መሰጠታቸውንም ማረጋገጥ፣ የሴት ልጆች ግርዛት እንዲቀር ማስተማር

9.5 ከሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚወጡ ጤና አገልግሎት ዕቅዶችን በማጣጣም አገልግሎቶቹን ማስተባበር፣ መቆጣጠር።

## አንቀጽ አሥር

### የፆታ እኩልነትና መብት ማስከበር

10.1 በፖለቲካ፣ በኤኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ኑሮ፣ በባህል፣ በትምህርት፣ በጤና አገልግሎት….ወዘተ በወንዶችና በሴቶች መካከል እኩልነት እንዲኖር ማድረግ፣

10.2 ለተመሳሳይ ሥራ እኩል ክፍያን ማረጋገጥ፣

10.3 የሴቶችን በማኅበር የመደራጀት መብት ማስከበር፣

10.4 ለማኅበራዊ ዕድገትና ነፃነት የሚስማሙ የጋብቻና የቤተሰብ ግንኙነት ሕጎችን ማውጣት፣ ሕግ በሚወሰነው መሠረት ለአቅመ-ሔዋን ያልደረሱ ልጃገረዶች እንዳያገቡ ማገድ፣ ሴቶች ወሊድን ለመቆጣጠር ያላቸውን መብት ማክበር፣ የሴት ልጆች ግርዛት እንዲቀር ማስተማር።

10.5 ሴተኛ አዳሪነትን ለማስቀረትና ለሴተኛ አዳሪነት መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች ለማስወገድ መጣር፣ ለሴተኛ አዳሪዎች ትምህርትና የሥራ ሥልጠና ለመስጠት መጣር፣

10.6 በኢትዮጵያ ገጠሮች የሴቶችን ሕይወት ለማሻሻል አስፈላጊ የሆኑትን የመጠጥ ውሃ ጉድጓዶችንና ቧንቧዎችን ወይም የመስኖ ቦዮችን፣ የእህል ወፍጮ ተከላ፣ የማገዶ አቅራቦቶች ቅድሚያ መስጠት፣ የሴቶችን መብት መከበሩን ማረጋገጥ።

## አንቀጽ አሥራ አንድ

**<u>የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ደኅንነትን መንከባከብ</u>**

11.1 የሀገሪቷ ወንዞች፣ ፏፏቴዎች፣ ሐይቆችና ኩሬዎች በሕዝብ ባለቤትነትና በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

11.2 የሀገሪቷ የተፈጥሮ ሀብት ማለትም የደን፣ የዱር አራዊቷ፣ የአፈሯ፣ የውሃዋ፣ የአየሯን ንጹህነት መጠበቅ፣ የሀገራችን የተፈጥሮ ውበትና ጤናማነት እንዲጠበቅ ከብክለት ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ፣ ሁኔታው በተባባሰባቸው አካባቢዎችም የተፈጥሮን ሚዛን ለመጠበቅ የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል፣ የወንዞች፣

የጅረቶች ንጽህና ማረጋገጥ፣ የአፈር መሸርሸርን መከላከል፣ የደን መመንጠር፣ መጋየት፣ ለመከላከል በመንግሥትና በሕዝብ ተሳትፎ ያላሰለሰ እርምጃ መውሰድ፣

11.3 የተፈጥሮ ሚዛን በከፍተኛ ደረጃ በተዛባበት አካባቢ የተለየ ትኩረት በመስጠት በሁኔታው ተጎጅ የሆነውን ሕዝብ ከተደጋጋሚ ረሃብ ለማዳን የተጠኑ እርምጃዎችን በሕዝብ ትብብር ተግባራዊ ማድረግ፣

11.4 ለዱር አራዊት ጥበቃ የተከለሉ ዘመናዊ መናፈሻዎችን ማቋቋም፣ ተቋቁመው ያሉትን በአግባቡ መያዝ፣ ህገ-ወጥ አደንንና የዱር ምንጠራን የሚከላከል የዱር አራዊት የደን ጥበቃ ተቋም መመሥረት፣

11.5 ወንዞች፣ ፏፏቴዎች፣ ሐይቆችና፣ ኩሬዎች በዕቅድና በአግባቡ ተፈጥሮን በማይጎዳ (በማያዛባ) መንገድ ለኅብረተሰቡ ጠቀሜታ እንዲውሉ ማድረግ፣ የውሃ ኃይል፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫዎችን እንዲሁም ሌሎች የኃይል ማመንጫ ዘዴዎችን በማስፋፋት የደን ጭፍጭፋን ለማስወገድ መጣር፣

11.6 የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ደህንነት ከመጠበቅ አንፃር ደንብ አውጥቶ ደንቡ በባለ ኢንዱስትሪዎች....ወዘተ እንዲከበር ማድረግ፣

11.7 ለተፈጥሮ ሀብትና ለአካባቢ ደኅንነት ጥበቃ ወጭም ሆነ ለአጠቃላይ የገቢ ምንጭነት የሕዝቦች ክብርና የሀገሪቱን ጥቅም በማይነካ መልኩ የጉብኝት ግልጋሎት (ቱሪዝም) ማበረታታት፣ ለቱሪዝም መስፋፋት የሚሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች (ሆቴሎች፣ መንገዶች...ወዘተ) እንዲሟሉ ለማድረግ መጣር፣

11.8 ስለተፈጥሮ ሀብትና ስለአካባቢ ደህንነት ጥበቃ አስፈላጊነት በሀገርአቀፍ ደረጃ ትምህርታዊ ዘመቻ ማካሄድ፣

11.9 ለዓለም የአየር ሙቀት መጨመር መንስዔ የሆኑትን ደን ማቃጠልና የመሳሰሉትን መከላከል፣

11.10 ተለዋጭ የኃይል ምንጮች እንደ ንፋስ ኃይል፣ የፀሐይ ሙቀት ኃይል፣ የመሳሰሉትን ጥናቶች ማበረታታትና መተግበር።

11.11 ከመኪናዎች የሚወጣው ጭስ ከባቢያዊ አየርን ከመበከሉ በተጨማሪ ለጤናም ጎጅ ስለሆነ መንግሥት በመኪናዎች ላይ ቁጥጥር እንዲያደርግ

## አንቀጽ አሥራ ሁለት

<u>የመከላከያ ኃይልን በተመለከተ</u>

12.1 በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የሠፈሩትን የሕዝቡን መብቶች የሚያከብር፣ እንዲሁም የሕዝቡን ፍላጎቶችና ጥቅም የሚጠበቅ የሀገሪቷን ድንበርና ሉዓላዊነት የሚከላከል የጦር ኃይልና የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታ የሚያስከብር የፖሊስ ሠራዊት መመሥረት፣

12.2 ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ያላገለለ አስፈላጊ መሥፈርቶችን በሚያሟላ መንገድ ተመልምሎ/ላና በፈቃደኝነት የተቀጠረ፣ ታዛዥነቱም በኢትዮጵያ ሕዝብ ለተመረጠ መንግሥት የሆነ ሙያተኛ ወታደራዊ ተቋም መመሥረት፣ ለሀገር ውስጥ ሰላምና ፀጥታ ጥበቃ ታዛዥነቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ለተመረጠ መንግሥት የሆነ ሙያተኛ የፖሊስ ተቋም መመሥረት፣

12.3 የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ኃይሉ በውጼታቸው (በፍላጎት) በሚቀጠሩ የጦር/የፖሊስ ኃይሎች አባላት ማቋቋም፣

12.4 የጦር ኃይሉ፣ የፖሊስ ሠራዊቱና የደህንነት አካሉ በፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ አይገቡም፤ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል አይሆኑም ታማኝነታቸው በሕዝብ ለተመረጠ መንግሥትና ለሕገመንግሥቱ ብቻ ነው፡፡

12.5 የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ አባላትና የደህንነት ሃይሎች በሀገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ በመምረጥና በውሳኔ-ሕዝብ በመሳተፍ ብቻ እንዲሆን ማድረግ፣

12.6 በጦር ኃይሎችና በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ የፖለቲካ ኃይሎችን እንቅስቃሴ ማገድ፣ ወታደሮችና ፖሊሶች የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት/ቡድን ወይም ስብስብ አባል እንዳይሆኑ በሕግ መደንገግ፣

12.7 በፖለቲካ ለመሳተፍ (የድርጅት አባል ለመሆን፣ ለመመረጥ) የሚፈልጉ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ አባሎች በቅድሚያ ከጦር ኃይሉ መሰናበት ይኖርባቸዋል፣

12.8 የጦርና የፖሊስ ሠራዊት አባሎችን ደህንነት መጠበቅ፣ የጡረታ መብታችውን ማስከበር፣ በግዳጅ ተሠማርተው ለተሰዉ መደበኛ ወታደሮችና የፖሊስ ሠራዊት አባላት ቤተሰቦች ተገቢ ዕርዳታና እንክብክቤ ማድረግ፣

12.9 በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ ሀገር የጦር ሠፈሮች እንዳይቋቋሙ በጥብቅ መከልከል፣

12.10 ከፌደራሉ አቅም በላይ የሚሆን የጦር ሐኃል በክፍል ሐገራት እንዳይቋቋም በህግ መከልከል

12.11 የሰራዊቱ አመራር ተዋፅዖ ሁሉንም ብሐረሰቦች ከግምት ወስጥ ያስገባ እንዲሆን መንግሥት ክትትል ያደርጋል።

## አንቀጽ አሥራ ሦስት

## <u>በሰላምና መከባበር ላይ የተመሠረተ፣ የኢትዮጵያን ጥቅም ያስጠበቀ የውጭ ፖሊሲን መከተል</u>

13.1 የኢትዮጵያን ጥቅም በማስጠበቅና በማስቀደም ላይ በመመሥረት በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ ኅብረት ማዕቀብ ከተጣለባቸው መንግሥታትና ኃይሎች በስተቀር ከሁሉም ሀገሮች ጋር በሰላም አብሮ መኖር፣ በእኩልነት በጋራ ጥቅም መሠረት ግንኙነት መመሥረት፣ ማጠናከር፣

13.2 ከጎረቤት አገሮች ጋር በሰላም የአብሮ መኖር መርኅ መከተል፣ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት፣ በብሔራዊ ጥቅሞችና ደህንነት ላይ በትብብር መሥራት፣

13.3 ኢትዮጵያ የገባቻቸውን የአካባቢ፣ አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ውሎች ፍትህዊነትና ሚዛናዊነት በመመርመር፣ በማሻሻልም እንዲከበሩ ማድረግ፣

13.4 ከአፍሪቃ ቀንድ ሀገሮች ጋር በቀጠናዊ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የፀጥታ ጉዳዮች ላይ በትብብር መሥራት፣

13.5 የአገር አቋራጭ ወንዞችን አጠቃቀም በተመለከተ የጋራ ጥቅሞችን ያማከሉና የዓለም አቀፍ የውሃ ሕጎችን ያገናዘቡ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ

13.6 ለአፍሪካ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር ከሚታገሉ ኃይሎች፣ ድርጅቶች፣ ሀገሮች ጋር በመተባበር የአፍሪካ ኅብረት የተለያዩ ዘርፎችን መደገፍ፣

13.7 የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም፣ የዜጎችን መብትና ክብር እንዲሁም ሀገራዊ ነፃነትና ልማት የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት መፍጠር፤

13.8 ከተለያዩ ሀገሮች ጋር በሚኖር ኝኙነት ወዳጅነትና ትብብር ኢኮኖሚያዊ ዕድገትንና ማሕበራዊ ፍትህን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፣

13.9 ለፍትኅ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለነፃነታቸውና ለሰብዓዊ መብት ለሚታገሉት ሕዝቦች ሁሉ የኢትዮጵያን ድጋፍ መግለጽ፣

13.10 ከኤርትራ ጋር በሰላማዊ ሁኔታ ውህደት የሚፈጠርበት አቅጣጫ መከተል፣

13.11 የባህር በር ካላቸው የጎረቤት ሀገራት ጋር በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት በመስማማት ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት የምትሆንበትን ሁኔታ መፍጠር

13.12 ኢ.ሕ.አ.ፓ የሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ በመሆኑ ከሶሻል ዴሞክራቶችና አገሮች ጋር ልዩ ወዳጅነትና ግንኙነትን ያደርጋል።

13.13 የኢትዮጵያ የውጪ ግኑኝነት ፖሊሲዎች ለዜጎች ቅድሚያ የሚሰጥ፣ የሀገር ኢኮኖሚ ጥቅምን ያማከለ እና የህዝብ ለህዝብ ግኑኝነትን ትኩረት የሚያደርግ እንዲሆን ማድረግ፣

## አንቀጽ አሥራ አራት

<u>ሰንደቅ ዓላማ</u>

14.1 ድንደቅ ዓላማችን ለዓመታት አባቶቻችንና እናቶቻችን በደማቸውና በአጥንታቸው ተንከባከበው ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፉልን ቅርስ ነው።

14.2 የሰንደቅ ዓላማችን ቀለማት ከላይ ወደታች አረንጓዴ ብጫና ቀይ ነው። ቀለማቱም የሚከተሉት ትርጉሞች መግለጫ ናቸው፦

አረንጓዴ - ያገሪቱን ልምላሜና ውበት፣
ቢጫ - በሰላም፣ በፍቅር ላይ የተመሠረት አንድነት፣
ቀይ - በአባቶችና እናቶች ተመሥርታ በጀግኖች ልጆቿ ደምና መስዋዕትነት አንድነቷና ድንበሯ እንደተከበረ፣

14.3 ሰንደቅ አላማችን በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ደምና አጥንት ለዕልፍ አዕላፍ ዓመታት ተከብሮ የኖረና የማንነታችን መግለጫ ስለሆነ ሊቀየር የሚችለው በውሳኔ-ሕዝብ (referendum) ብቻ ነው።

-----///-----